Institute of Development &
Education for Africa, Inc.

# ኢ.ሕአሠ
# (የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት)
# ከ1964 — 1970 ዓ.ም.
## ቅጽ አንድ
## በ አስማማው ኃይሉ
## 2003 ዓ.ም.
## አቃቂር፡ በ ገላውዴዎስ አርኣያ
## June 14, 2011

ደራሲው መጽሓፉን ለአንባቢያን ለማቅረብ የገፋፉት ምክንያቶች አምስት ሲሆኑ ከነዚሁ ሁለቱ የሚከተሉት ናቸው፡ 1) "የኢ.ሕአሠን ታሪክ በሚመለከት እስከ ዛሬ በጥቂቱም ቢሆን መረጃዎችን ያዘሉ ጽሑፎች ባለመቅረባቸው" እና 2) እውቀቱና ፍላጎቱ ያላቸውም ቢሆን ስላሳለፉት የትግል ታሪክና ሊያበረክት ስለሚችለው አስተዋጽኦ በተለያዩ ምክንያቶች ሊያሚሉ አለመቻላቸው።"

ትክክለኛ አባባል ነው። ነገር ግን አጋጣሚ ሆኖ ደራሲው ሳያገኘው ቀርቶ ሊሆን ይችላል እንጂ እኔ በ1995 እአአ Ethiopia: The Political Economy of Transition በተሰኘው መጽሓፌ ውስጥ በምዕራፍ 4 The Ethiopian Peoples Revolutionary Party (EPRP) and The Ethiopian Left በሚል ርእስ የኢ.ሕአፓ መሠረትና መነሻ፣ የኢ.ሕአፓ የፖለቲካ ክንውኖች፣ ኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት፣ ኢ.ሕአፓና ህወሓት፣ ኢ.ሕአፓና መኢሶን፣ ኢ.ሕአፓ፡ ኦነግ፡ ኢ.ሕዴን፡ እና የኤርትራ ግንባሮች፣ እና የኢ.ሕአፓ ጠንካራና ደካማ ጎኖች የሚሉት ርእሰ-ነገሮችን ከሞላ ጎደል ለአንባቢ አቅርቢያለሁ።

እንደተመኘነው ሁሉ፡ በሕብረተሳባችን ዘንድ የጥናትና ምርምር ባህል ማደግና መስፋፋት ባለመቻሉ፡ ገናም በእንጭጭነቱ ስለሚገኝ፡ በዛው መጠንም የማንበብ ባህል ማደግ ስላልቻለ መጻሕፍት ቤቶችና መደብሮችን የሚያዘወትሩ ቀለም የቀመሱ ኢትዮጵያውያን ቊጥራቸው አነስተኛ ነው። የማንበብ ባህል ካዳበሩ ግለሰቦችም ገሚሱ በየመንገዱና በየሱቅ ቤቶች ወይም እንጀራ ቤቶች የሚያገኟቸው መጻሕፍት ብቻ ነው የሚያነቡት።

ከላይ ካቀረብኩት ትችት ባሻገር ግን የደራሲው ዋና መልእክት፡ በህይወት እያለን የምናውቀውን ያህል በጽሑፍ/መጽሓፍ መልክ ብናቀርብ ለመጪው ትውልድ ቅርስ እንተዋለን የሚል መሆኑን ማንኛውም በጥሞና የሚያነብ አንባቢ መገንዘብ ይችላል። ከዚህም መንፈስ በመነሳት ነው ይኸንን አቃቂር ማበርከት የፈለግኩት። አጋጣሚውን በመጠቀም ደግሞ አቶ አስማማው ኃይሉ ላደረገው ግዙፍ አስተዋጽኦ የላቀ ምስጋናየን ላቀርብለት እፈልጋለሁ።

ሌሎች በትግል ዙርያ የነበሩ ኢትዮጵያውያን፡ ‘ማን ያውራ የነበራ፡ ማን ያርዳ የቀበረ’ ነውና፡ የተቻላቸውን ያህል እንድያበረክቱ አደራ እላለሁ። ለምሳሌ በገጽ 14 የኢትዮጵያ አውሮጳ ተማሪዎች ማሕበር አስመልክቶ እነ ኃይሌ ፊዳ እና እነ ደሳለኝ ራሕማቶ ተጠቅሰዋል። ኃይሌ ፊዳ በመጠኑም ቢሆን ስለፍልስፍና እና ርእዮተ ዓለም ከመጻፉም በላይ መጻሕፍት መደብርም ለአንባብያን አቅርቦ ነበር። ነገር ግን ጭራቂ ደርግ ስለቀጨው ለሕብረተሰቡ ማቅረብ የነበረበትን እውቀትና ማሕበራዊ አገልግሎት ከእርሱ ጋር ተቀብረዋል። ደሳለኝ ራሕማቶ ግን በሕይወት ስለሚገኝ ከዚህ ቀደም ካደረጋቸው ጠቃሚና ገንቢ የጥናትና ምርምር ጽሑፎች (መጻሕፍትም ጭምር) ለጥቆ የተማሪውን ንቅናቄና ከየካቲት አብዮት ፍንዳታ በኋላ የተካሄደውን ትግል አስመልክቶ ቢጽፍ መልካም አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ጥርጥር የለውም።

አንድ አቃቂር የሚጽፍ ተቺ በመሠረቱ ስለ መጽሓፉ ይዘትና መልእክት ከተቻለም ውስጠ ወይራውን መመርመር እንጂ ስለ ራሱ ተሞክሮዎችና ድርጊቶች መጻፍ የለበትም። ከዚህ ቀደም የጻፍኳቸው አቃቂሮችም ይኸንን መርሕ በመከተል ነው። ይህ መጽሓፍ ግን የብዙ ጓዶች (የኔም ጭምር) ተመክሮዎች በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ ስለዘገበው በመጠኑም ቢሆን የመጽሓፉን ይዘት ለማጉልመስ ያህል ስለራሴ ተሞክሮዎችና አመለካከቶች ማቅረብ የግዴታ ይሆናል።

ይህ መጽሓፍ በይዘቱ ከሌሎች መጻሕፍት ለየት የሚያደርገው ነገር ቢኖር ደራሲው የራሱ አመለካከት፡ ትችትና ትንተና ሳይሆን ልዩ ልዩ የኢሕአፓ/ሠ ተዋንያን (በድርጅቱ በተለያየ ደረጃ የተሳተፉት ተጋዳዮች) ያቀረቡለትን ዘገባ ወይም በቃለ መጠይቅ ያጠናቀራቸውን መረጃዎች አመቻችቶ ለአንባቢ ማቅረቡ ነው። ለምሳሌ ከገጽ 35 እስከ ገጽ 37 እንዲሁም በገጽ 38 ጸሐየ፡ ሮባ እና ጌራ ስለ ብርሃነመስቀል ረዳ ጠንካራና ደካማ ጎኑ በሚመለከት ያቀረቡትን ትችት ትክክል ይመስለኛል። እኔ ብርሃነመስቀልን በዝና ነው የማውቀው እንጂ በአካል አይቸው አላውቅም። ዘርኡ ክሕሸን ከመሞቱ በፊት ግን ንውዮርክ መጥቶ ነበረና ኢትዮጵያን አስመልክቶ ዓበይት ነጥቦችን በማንሳት በሰፊው ተወያይተን ስለነበር፡ ከመሃሉ የብርሃነመስቀል ጉዳይ ተነስቶ ያለውን አመለካከት ስጠይቀው ጸሐየ፡ ሮባ እና ጌራ የሰጡትን አስተያየት ዓይነት ነው የሰጠኝ። ያም ሆኖ ይህ ግን፡ የፈለገውን ልዩነቶች ይኑሩ፡ ብርሃነመስቀል በደርግ ከተረሸነ በኋላ የኢሕአፓ መጽሔት ‘አብዮት’ Death of A Renegade (የከዳተኛ ሞት) ብሎ ማውጣቱ ቅር አሰኝቶኝ ስለነበረ ከፍ ብዬ በጠቀስኩት መጽሐፌ ውስጥ በነቀፌታ መልክ ጠቅሼዋለሁ።

በገጽ 44-45 ብርሃነመስቀል በኤርትራ የነበረውን ወይም የወሰደውን አቋም አስመልክቶ ጌራ ካቀረባቸው ዘገባዎች አንዱ እንዲህ ይላል፦ “ብርሃነመስቀል ረዳ አራግ ላይ በተደረገው ውይይት ‘የኤርትራን ጥያቄ በነጻነት ጥያቄ መቀበል አለብን። እኔ እራሴ የፓርቲው ዋና ጸሐፊነት ቦታዬን መስዋዕት አድርጌም ቢሆን እስከምችለው ድረስ እገፋበታለሁ። እናንተም በእዚህ አቋም ላይ ግልጽ ውሳኔ ላይ መድረስ አለባችሁ’ በማለት አሳስቦ ነበር።”

እኔ የሰማሁት ደግሞ ከዚሁ የተለዬ ነው። እኔና ስድስት ሌሎች ጓዶች ሳሕል ቆይተን ወደ ዓሲምባ ለመሄድ ዝግጅት በምናደርግበት ጊዜ ብሌቓት አከባቢ የህግሓኤ የድኅንነት (ክፍሊ ጸጥታ) ሓላፊ የነበረውን ኃይለ ጀብሃ የሚባል “ብርሃነመስቀልን በኤርትራ ያለውን አቋም ጠይቀነው በንቀት መልክ ነው የመለሰልን፣ በብጣሽ ወረቀት የኢትዮጵያ ካርታ ከሳለ በኋላ የኢትዮጵያና ኤርትራ

ድንበር በዚሁ ወረቀት አካለለና ከፈለጋችሁ መሄድ ትችላላችሁ ብሎ ወረቀቱን ወረወረልን" በማለት አጫውቶኛል።

በገጽ 50 የኢ.ሕአፓ/ሠ የመጀመርያ ተጋዳዮች "አሲንባ እንደገቡ ሕብረተሰቡን ለመቀላቀል ጊዜ ፈጅቶባቸዋል" የሚለውን ሓረግ ትክክል ሆኖ፣ "በማያውቃቸው ሕዝብ መካከል ተዋሕዶ ለመኖር የሚያስችል ግንኙነት ባለመኖሩ ባብዛኛው የመጀመርያ ወራት መደበቅን ይመርጡ ነበር" የሚለውን ግን ሙሉ በሙሉ ለመቀበል ያስቸግራል። ዓሲምባ ኢ.ሕአሠ እግሩን የሚተክልበት አካባቢ ሆኖ የተመረጠበት ምክንያት ከመልክአ ምድሩ አቀማመጥ (ለሽምቅ ውግያ አመቺነት)፡ ከሕዝቡ (በተለይም የዓዲ ኢሮብ) ተአማኒነት እና ለኤርትራ ቅርብነት ብቻ ሳይሆን ከኢ.ሕአፓ/ሠ ቀንደኛ የአመራር አባላት የትግራይ ተወላጆች ሆኖው በርካታው ከዓጋመ አውራጃ የመነጩ ስለነበር ከሕዝቡ ጋር ትውውቅ ስለነበራቸው ጭምርም ነው። ይኸንን እውነታ የሚደግፍ ዘርኡ ክሕሸን እንዲህ ብሎ አጫውቶኝ ነበር፦ "ከዕለታት አንድ ቀን በአንድ መንደር ከሕዝቡ እየተወያየን እያለን ድንገት የሩቅ ዘመዴ የሆነችው አንዲት ሴት ወደ ነበርንበት መጣችና፡ ቀስ በቀስ ወደኔ እየተጠጋች 'አንተ ዘርኣይ አይደለህም እንዴ? በፈገግታህ እኮ ነው ያወቅኩህ' አለችኝ። ተደብቆ መደበቅ አይቻልም።"

በገጽ 52 ሮባ ስለ ዓዲ ኢሮብ ሕዝብ "በኢትዮጵያውነቱ የማይደራደር ሕብረተሰብ ነው" ማለቱ ትክክል ሲሆን "አብዛኞቹ የካቶሊክ ኃይማኖት ተከታዮች" ናቸው ብሎ በማያሻማና በእርግጠኝነት መናገር ግን አይቻልም። እኔም በበኩሌ ተመሳሳይ አመለካከት ነው የነበረኝ። ነገር ግን ደንቨር (ኮሎራዶ) ከሚኖሩት የዓዲ ኢሮብ ተወላጆች "የተወሕዶ ኃይማኖት ተከታቶች ይበዛሉ" ብለውኝ ነበር። በእርግጥ በትግራይ በርካታው የካቶሊክ ምእመናን በዚሁ በዓዲ ኢሮብ ነው የሚገኙት፣ ግን በቅጡ የቀረበ የስነ-ሕዝብ (demographic) ጥናት የለም።

በገጽ 54 ሮባ "አስገድዶ ምግብ ማግኘት ከዓለማችን አንጻር የተከለከለ በመሆኑ የድርጅታችን ሥነ-ምግባር ለማንነታችን የመጀመርያ መረጃ ነበር" ያለውን ትክክል ሆኖ እንድያውም ይኸ የሠራዊቱ ሥነ-ምግባር የሕዝቡን ድጋፍ የሚገኝበትን ሁኔታ ፈጥሮ ነበር የሚል እምነት አለኝ። ሥነ-ምግባሩ እስከ መጨረሻ፡ ማለትም ሠራዊቱ በትግራይ መሬት እስከ ቆየ ድረስ፡ ነው የቀጠለው። ኢ.ሕአሠ ከአርሶ አደሩ ምግብ ይገዛ ነበር፣ አልፎ አልፎ ግን ሕዝቡ በራሱ አነሳሽነትና ፈቃደኝነት ምግብ (ጥራምሬ፡ ቂጣ፡ እንጀራና ወጥ) ለሠራዊቱ ያቀርብ ነበር።

በገጽ 62 "ዶክተር ተስፋዬ ደበሳይና ብርሃነመስቀል ለፓርቲው ቀጣይ ጉባኤ ወደ አዲስ አበባ ከሄዱ በኋላ ከሠራዊቱ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት አልነበረም" የሚለውን ትዝብት ሙሉ በሙሉ የምስማማበት ጉዳይ ነው። ኢ.ሕአፓ ድል እንዳይቀዳጅ ካደረጉት አንዱ ምክንያት የከተማን ትግል ቀዳሚነት በመስጠትና ለኢ.ሕአሠም አስፈላጊውን ትኩረት ባለመስጠቱ ነው። የኢ.ሕአፓ ድል ያለመቀዳጀት ወይም መውደቅ ግን በዚሁ ብቻ የሚገለጽ አይሆንም፣ እጅግ በጣም የተወሳሰበ ነው። ከላይ የተጠቀሰውን ድክመት ብቻ ሳይሆን በውስጡም የመነጣጠል ባሕርያት (አንጃኝነት) በመከሰታቸው፣ ሰርጎ ገቦች በፓርቲውና በሠራዊቱ በመንቀሳቀሳቸው፣ ደርግ በኢ.ሕአፓ ከፍተኛ ጉዳት በማድረሱ (በተለይ በቀይ ሽብር ጊዜ)፣ የኤርትራ ግንባሮች በጎ ነው ከተባለ በጥርጥሬና በዓይነ ቁራኛነት፡ መጥፎ ነው ከተባለ ደግሞ በጠላትነት ኢ.ሕአፓን ስለፈረጁትና፡ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉም በነዚህ ችግሮች ላይ ሕወሓት በጦርነት ኢ.ሕአሠን ከትግራይ ለማስወገድ ማቀዱና መብቃቱ ነው የሕአፓን ውድቀት ያቀላጠፈው። የሚገርም ነገር ቢኖር ግን ከዚህ ሁሉ ውርጅብኝ በኋላ ኢ.ሕአፓ/ሠ ከፍተኛ መስዋእትነት ቢከፍልም ቅሉ

ሙሉ በሙሉ ያለመጥፋቱ ነው። ድርጅቱ እንደ የዱር አጋዘን በአንበሶች፣ ነብሮች፣ ጅቦችና የሜዳ ውሾች ተከቦ እያንዳንዱ አራዊት በየተራ ከቦጫጨሩት በኋላ እንደምንም ብሎ አምልጦ የተረፈ እንስሳ ነው የሚመስለው።

ቀደም ብሎ የተጠቀሰውን የኢሕአሠ ሥነ-ምግባርና ከሕዝቡ ጋር የነበረው መልካም ግንኙነት ደራሲው እንደገና በገጽ 127 አብራርቶታል። ከዚሁ ጋር በማያያዝም “አብዛኛው የትግራይ ሕዝብ የታጠቀ አልነበረምና በሠራዊቱ ላይ በቡድን ዘምቶ ጉዳት አላደረሰም። የትግራይ ሕዝብ በበሽታ የተዳከሙና በጦርነት የቆሰሉ የሠራዊት አባላትን በመደበቅና በማስታመም ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል” ይላል። የትግራይ ሕዝብ እንደ ሌሎቹ የኢትዮጵያ ብሔራት ጨዋ ሕዝብ ነው። ምናልባት የትግራይን ሕዝብ አወንታዊ ሚና ለየት የሚያደርገው ነገር ቢኖር ግን ለዘመናት ሲያደርገው በመቆየቱ ነው፣ ይኸም የሆነበት ምክንያት ትግራይ የጥንት የኢትዮጵያ ስልጣኔ መናኸርያ ከመሆኑም በላይ የአገሪቷ ሰሜናዊ ክፍለ-ሃገር ከመሆኑም በላይ ለቀይ ባሕር ቅርብነት ስላለው የኢትዮጵያ ጠላቶች በየጊዜው በዛ በኩል ጥቃት መሰንዘራቸው ነው። ስለሆነም በአፄ የሐንስ ጊዜ በጉንደትና በጉራዕ ከግብጾች ጋር በተካሄዱት ጦርነቶች፣ በሰሓቲና በዶግዓሊ (በራስ አሉላ መሪነት) ከጣልያን ጋር በተደረጉት ጦርነቶች፣ በመተማ ከድርቡሾች ጋር በተደረገው ጦርነት፣ በአፄ ምንሊክ ጊዜ በዓድዋ ከጣልያን ጋር በተደረገው ጦርነት፣ በአፄ ኃይለሥላሴ ጊዜ በማይጨው እና በተምቤን ከጣልያን ጋር በተደረጉት ጦርነቶች የትግራይ ሕዝብ የኢትዮጵያን ነጻነት ለማስጠበቅ ከፍተኛ መስዋእትነት ከፍሏል።

በገጽ 130ና በገጽ 131 ‘የትግል ቋንቋዎች’ን አስመልክቶ ደራሲው በትክክል አስቀምጦታል። የትግሉ ቋንቋ ትግርኛ መሆኑ ነው። ‘መፈናተት’ (በሰልፍ ላይ ርቀትን መጠበቅ)፣ ‘አብሩክ’ (ተንቆርጥጦ መቀመጥ)፣ ‘ተበገስ’ (ተንቀሳቀስ)፣ ‘መስርዕ’ (የሰልፍ መስመር)፣ ‘ተሸክል’ (ምሽግ)፣ ‘ህጁም’ (የጨበጣ ውግያ) ወዘተ። በርካታ የኢሕአሠ ሠራዊት አባለት ግን ከዚሁ ከግብራዊ ስያሜዎች አልፈው የትግርኛ ቋንቋን ማቀላጠፍ የጀመሩ ስለነበሩ ከሕዝቡ ጋር በቀላሉ ለመግባባትና ለመቆራኘት በቅተው ነበር። ይህ በአንድ በኩል ኢሕአሠን ጥሩ ውጤት ቢያስገኝለትም የሠራዊቱ ጠላቶች ግን ማስበርገጉ አልቀረም፣ ከትግራይ የሚወጣበት ሴራ የተጠነሰሰውም በዚሁ ምክንያት (ሌሎችም ሰበቦች እንዳሉ ሆነው) ይመስለኛል።

በገጽ 138 አማኑኤል እንደዘገበው በአንድ የሕወሓት ኃይልና በአንድ የኢሕአሠ ኃይል (ኃይል 3) “ሰላም የሰፈነበት” አመርቂ ውይይት መካሄዱን ገልጾታል። የተነሱት የመወያያ ነጥቦች ደግሞ 1) ከብሔርና ከመደብ ትግል የትኛው መቅደም እንዳለበት፣ 2) በብሔር ትግል ሥር ቡርጂ፣ ላብ አደሩ፣ ፊውዳሉ፣ አርሦ አደሩና አድሐሪ ንዑስ ከበርቴዎች ስለሚሳተፉ ከነጻነት በኋላ በምን ዓይነት ሁለንተናዊ ፖሊሲ ከላይ የተጠቀሱትን ተጻራሪ መደቦች በጋራ ማስተናገድ ይቻላል በሚልና 3) በኤርትራ ጥያቄ።”

እንዲህ ዓይነት የሰለጠነ ውይይት በሁለቱ ሠራዊቶች መሃከል መካሄዱ አማኑኤልን ብቻ ሳይሆን ሁላችንም ያስገረመን ነገር ነው። ዘለቄታ እንደማይረኖው ግን ገና ለገና መገመት ተችሎ ነበር። ከዚሁ አንጻር በኢሕአፓ/ሠ በኩል ሕብረተሰቡን አስመልክቶ የአንትሮፖሊጂ ጥናቶች ስላልተካሄዱና ደጋፊ የፖለቲካና ርእዮተዓለማዊ መመርያዎች ደግሞ ለሠራዊቱ ባለመቅረባቸው የሚያጋጥመው ማንኛውም የሚቃረንና የሚጋጭ ክስተት በምን መልኩ መፈታት እንዳለበት በቅጡ ማወቅ አልተቻለም ነበር። ቁጭ ብሎ የመወያየት ባህልና ችግሮችን በሰላም መፍታት ጥንት በሕብረተሰባችን ቢኖርም ቅሉ በኛ ትውልድ (ዘመን) ግን ደብዛው

ከጠፋ ቆይቷል። ለዚህም ነው በድርጅቶች ዘንድ የመናቆርና የመጠፋፋት እርምጃዎች የተከሰቱት።

ከየካቲት ’66 አብዮት ፍንዳታ በፊት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ይሁን በአብዮቱ ሂደት ጊዜ ውስጥ የተፈጠሩት አገር-አቀፍ ድርጅቶች (ኢሕአፓ፡ መኢሶን ወዘተ) እና የብሔር ድርጅቶች (ህወሓት፡ ኦነግ ወዘተ) ግፋ ቢል የማርክስ-ሌኒንነት ርእዮተዓለም ብቻ (እሱም ቢሆን ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በማይዛመድ መንገድ) በማራመድ በመደብ ትንተናና ብሔር-ነክ ገለጻዎች ብቻ ነበር የኢትዮጵያን ሕብረተሰብ የመዘኑት። ሌሎች ዓበይት በሀርያት እንደ ኃይማኖት፡ ባህል፡ ተቋሞች፡ ታሪክ፡ ንቃተ-ኅሊና፡ የሰው (በግል ወይም በቡድን) ዝንባሌዎችና ፍላጎቶች ወዘተ በግምት ውስጥ አላስገቧቸውም ነበር። አሁን ደግሞ ይባሱኑ ያሉት የፖለቲካና የሲቪክ ማሕበራት ከናካቴው ከተጠቀሱት ርእዮተ-ዓለም እና ባህርያት እጅግ በመራቅ በጥቃቅን የጎጥ ፖለቲካ ስለሰመጡ የኢትዮጵያችን ጉዳይ እጅግ በጣም አሳሳቢ ሆኗል።

በገጽ 141 እና 142 ሳጅግ የቤጌምድር ኢሕአሠን አስመልክቶ የተወሳሰበውን የፖለቲካ ጉዳይና ያስከተለውን የወታደራዊ እንቅስቀሴ ስህተቶች ያቀረበው ዘገባ በጣም አመርቂ ከመሆኑም በላይ፡ መደነቅ ያለበትና አውነትነትን የሚያንጸባርቅ ሓተታና ትንታኔ (ትዝብት) ስለሆነ፡ ለወደፊት ተጨማሪ ጥናት ከተካሄደ ተደብቆ የነበረውን ሚስጢር ሊከሰት ይችላል።

በገጽ 154 አቶ አስማማው ስለ ጋንታ 44 ድርጊት ሲያወሳ፡ “የጋንታ አርባ አራት የጥበቃና የምርመራ አባላት ጭካኔ የተሞላባቸው የምርመራ ዘይቤዎችን ሲጠቀሙ እርሕራሔ አልንበራቸውም” ከማለቱም በላይ በገጽ 155 ደግሞ “ምርመራው እጅና እግርን አስሮ ወደ ኋላ ከገለበጡ በኋላ የውስጥ እግርን በደረቅ ዱላ ከመቀጥቀጥ ባሻገር በጋለ ሳንጃ ጀርባን መተኰስንም ያካተተ ነበር” ይላል። ያሳዝናል በጣም! ታድያ ለፍትሕና ለዴሞክራሲ የሚታገል ድርጅት ኢሰብአዊ ድርጊቶችን በሕቡእ የሚፈጽም ከሆነ ምን ዓይነት ሕብረተሰብ ሊኖረን ነበር ሥልጣኑ ቢያዝ ኖሮ?

በተጨማሪም፡ ደራሲው ታስረው ከነበሩት ሰዎች አንዳንዱን ይጠቅስና የሚከተሉትን የስም ዝርዝር ያቀርባል፦ 1) ጌታሁን ሲሳይ፡ 2) አስማማው ኃይሉ (ደራሲው)፡ 3) ሃብቶም፡ 4) አያሌው ይማም፡ 5) አያሌው መርግያ (ስዒድ)፡ 6) አዲስዓለም እና 7) የመቶ አለቃ በሪሁን። የነዚህ ጓዶች የጋንታ 44 ሰለባ መሆን የኢሕአሠ አባለት ተጠያቂ አይሆኑም፣ በስቃይ ቅጣት የተሰማሩ ግለሰቦችና የኢሕአፓ/ሠ አመራር ግን በሕግ ፊት ተጠያቂ ናቸው። ይኸንን አስጸያፊ ድርጊት አስመልክቶ እግረ መንገዴን ሁለት ነገሮች ማንሳት እወዳለሁ፦ 1) ከሰለባዎቹ አንዱ ደራሲው አስማማው ሆኖ ያለ ቅሬታና ቂም በቀል ይኸንን መጽሓፍ አጠናቅሮ ማቅረቡ እጅግ በጣም መመስገን አለበት፣ 2) የጋንታ 44 ጉድ አስመልክቶ ከሰለባዎቹ ሌላው አቶ አያሌው ይማም በቅርቡ ታትሞ የወጣውን መጽሓፉ ውስጥ በዝርዝር አስቀምጦታል።

ጋንታ 44 እንደ ድኅንነት ጠባቂ እንጂ አረሜናዊ ተግባራትን የሚያካሂድ ለመኖሩ የሚያውቅ የሠራዊቱ አባል ያለ አይመስለኝም፣ ከጋንታውና ከአመራሩ በስተቀረ። ነገር ግን ደራሲው በቅደም ተከተል ያስቀመጣቸውን የታሰሩትን ሰዎች ስሞች በአንድ ቦታ ላይ የታሰሩ አልመሰለኝም። ይኸን ያልኩበት ምክንያት ደግሞ መጽሐፉን ካነበብኩ በኋላ አያሌው ይማምን ጠይቄው “ባንድ ላይ አልነበርንም” በሎኛል። በዚህም ላይ፡ እኔ ክፍለ ዜና ከእነ ገለብ ጋር በነበርኩበት ጊዜ ጌታሁን ሲሳይ (ግሩሙ) ከኛ ጋር ነበር የቆየው። በዛን ጊዜ ጌታሁን እስረኛ መሆኑን

አላውቅም ነበር፣ ምክንያቱም ነጻ ሆኖ በሰንገደ ይንቀሳቀስ ስለነበረና ደራሲው እንደጠቀሰው ደግሞ የአስም በሽታ ስለነበረው በዛ ምክንያት ከኛ ጋር እንዲቆይ የተደረገ መስሎኝ ነበር። ትንሽ የጠረጠርኩት ነገር ቢኖር ግን እኛ 'ዓሲምባ' የተሰኘውን ጋዜጣ በምናዘጋጅበትና በምንወያይበት ጊዜ ጌታሁን ምንም ዓይነት ተሳትፎ ስላልነበረው በግዞት መልክ የተገለለ መስሎኝ ነበር። እሱም አልተናገረም፣ ገለብም አልተናገረም! የኢሕአፓ ሚስጢር የበዳዩና የተበዳዩ ስነ-ልቦና ተቆጣጥሮ ነበር ማለት ይቻላል። አሁን ወደኋላ ተመልሼ ሳየው የሚገርመኝ ነገር ቢኖር ግን ኢያሴው ይማም እንዳደረገው ጌታሁን ሲሳይ ጨለማን ተገን በማድረግ ከነበረበት ጠፍቶ ህይወቱን ማትረፍ ለምን እንደ አቃተው ነው። እጁና እግሩ አልታሰሩም ነበር ፣ መንገዱንም ያውቀዋል። ለዚሁ ስንክሳር መልስ ማግኘት ይከብዳል፣ ምስኪኑ ጌታሁን በህይወት የለምና!

በኢሕአሠ ሠራዊት አነሳሽነት የተጀመረውን የግንቦት 1969 የእርማት እንቅስቃሴ በኢህአፓና በኢሕአሠ የሚደረግቱን ያሰራርና የአመራር ስሕተቶችን ለማረም ያቀደ ነበር። ነገር ግን በገጽ 173 እንደተገለጸው "በአያሌ የድርጅታችን አባላት ደም የተገነባው ኢ.ሕአፓ ለመታረምና ለመስተካከል ፈቃደኛ ባልሆኑ ያመራር አባላት ወደ ውድቀት እያመራ በመሆኑ የእያንዳንዳችን ብሩህ ተሳትፎ ይጠይቃል" የሚለውን የቀስቃሹ ጥሪ ከኔ አመለካከት ጋር የሚገጥም ብቻ ሳይሆን እንደ አጋጣሚም በተመሳሳይ መልኩ በመጽሓፌ ያሰቀመጥኩት ነገር ነው።

በገጽ 179-180 ስለ ኃይል 27 እና ኃይል 10 የወሎ ጉዞ ተጠቅሷል። እኔ የኃይል 27 ኮሚሳር ስለነበርኩኝ ጉዞውንና ሠራዊቱ ያጋጠሙትን ችግሮች በሚመለከት አበጥሬ የማውቀው ጉዳይ ነው። ስለሆነም በመጽሓፉ ያልተጠቀሱትን አንዳንድ ክስተቶችና ክንውኖች ለማከል ያህል ላቅርብና የወሎን ነገር በትችት እደመድመዋለሁ።

ሁለቱ ኃይሎች ወደ ወሎ ጉዞ ከመጀመራቸው በፊት የኢሕአሠ የበላይ አመራር ለእርማት እንቅስቀሴው ምላሽ እንደሰጠና ከወሰዳቸውም እርምጃዎች አንዱ ጌራን ከነበረበት የአመራር ሥልጣን አውርዶ የኃይል መሪ ብቻ እንዲሆን ማድረጉን በሰፊው ተወርቶ ነበር። ለሠራዊቱ ግን በግልጽ የተነገረው ነገር ስላልነበረ ነገሮችን ከመተርጐም አልፎ ግዳጁን ለመፈጸም ዝግጁ በመሆኑ ከዓሲምባ ወደ ወሎ ጉዞውን ጀመረ። ሁለቱ ኃይሎች እምብዛም ሳይራራቁ የተለመደውን የእግር ጉዞ ተያያዙት። ኃይል 27 ዓቢ ዓዲ (ተምቤን) አከባቢ እንደደረሰች ዓዲ ንፋስ በተባለው መንደር አጠገብ ሦስቱ ጋንታዎች እንድያርፉ ተወሰነ። ሁለቱ ጋንታዎች ከፍተኛ ከረብታማ ቦታ ይዘዋል፣ ሦስተኛዋ ግን መንደሩ አጠገብ ያለውን ዝቅተኛ ቦታ ይዛለች። ይኸም የሆነበት ምክንያት ደግሞ ሁለቱ ኃይሎች የጠላትን እንቀስቃሴ ለመከታተል ግዳጅ ሲሰጣቸው ሦስተኛዋ ደግሞ የአካባቢውን ሕዝብ ለመቀስቀስ እንድትሰማራ ኃላፊነት ተሰጥቷት ሰለነበረ ነው።

ግን ድንገት ደራሽ ነበልባል የተባለውን የደርግ ሠራዊት ከመቐለ ተነስቶ በሳምረ በኩል ይመጣና ጋንታዋን እንደ መክበብ ያደርጋል፣ የጋንታዋ መሪዎች የነበልባል መጠጋት ስለተገነዘቡ ወድያውኑ ተጋዳዮቹን ተሸክል ያስይዙና የሬድዮ መልእክትም ለሁለቱ ጋንታዎች ያስተላልፋሉ። በመልእክቱ መሰረት ሁለቱ ጋንታዎች የነበሩባቸውን ቦታዎች ለቀው ወደ ጋንታዋ ይጠጉና ነበልባልን ይከባሉ። ነበልባል ጋንታዋን ከቦ ለማጥፋት ተኵስ ለመክፈት ሲዘጋጅ ከግራና ከቀኝ ተኩስ ስለተከፈተበት እግሬ አውጭውኝ ብሎ ፈረጠጠ። ጋንታዋ ደግሞ ከመዓቱ ወጣች።

ከዛ በኋላ ሦስቱ ጋንታዎች በተቀናጀ መልክ ጉዛቸውን ቀጠሉ። አበርግለን አቋርጠን የወሎና ትግራይን ድንበር እንደደረስን የጽራሌ (የተከዜ ገባር ወንዝ) ቆርጠን የወሎ ዳገቶቹን ከመጋፈጣችን በፊት የኃይሏ ጓዶች እንድያርፉና እንዲጸዳዱ ተደረገና ጨዋታ ቀለጠ። በጨዋታው መሃል ተከባ ከነበረችው ጋንታ አንዳንድ ጓዶች ሕዝቡን ከማስተማር አልፈው ምግብ መግዛት ስለነበረባቸው መንደሩ ውስጥ በመግባት ያገኟዋቸውን ሴቶች "ዕልቦ (በቆሎ) መግዛት እንፈልጋለን" ባሉ ቍጥር ሴቶቹ እየተሽኰረመሙ ይርቋቸው እንደነበር አጫወቱን። ጓዶቹ ያላወቁት ነገር ቢኖር 'ዕልቦ' (ዕፉን) ማለት በትግርኛ 'በቆሎ' ሲሆን በተምቤን አከባቢ ግን ተጨማሪ ፍቺ ይሰጠውና ሁለተኛ ትርጉሙ "የሴት ብልት" ማለት ነው። ሴቶቹ የፈረጠቱት ያለምክንያት አይደለም።

ጽራሌ ሞልቶ ስለነበር ጉርፉ ቀለል ወዳለ አካበቢ ነበር ያቋረጥነው። ከዛ በኋላ ወደ ሰማይ ያነጣጠረውን፡ ማለቅያ ያለው የማይመስል፡ አቀበትን ተያያዝነው፣ መንሸራተትትና መላላጥ መጣ፣ ሠራዊቱ ግን መንፈሰ-ጠንካራ ስለነበር በሚያስደንቅ ሁኔታ ጉዞውን አገባደደ፣ ምቁን ማርያም ከተባለችው አነስተኛ የሰቆጣ ወረዳ መንደር (የገጠር ከተማ) ውስጥ ገባ። ከሕዝቡ ጋር ተገናኘ፣ ሕዝቡንም ማስተማር ጀመረ። የአካባቢው ሕዝብ ወግ አጥባቂ ክርስትያን ስለሆነ የሠራዊቱ አባላት ሲጃራ ከማጤስ እንዲቆጠቡ፣ ከተቻለም ማተብ በአንገታቸው እንዲያስሩ ተነግሯቸው ነበር። ይህ በእንዲህ እንዳለ እኔ በነበርኩበት አካባቢ አንድ በግምት ወደ 80 የሚጠጋቸው ሽማግሌ ከነምርኩሳቸው እየተራመዱ ወደኛ ተጠጉና "እናንተ'ማ ደርጎች አይደላችሁም" አሉን፣ "አይ፡ ስማችን ኢሕአፓ ነው፡ ደርግን የምንቃወም የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ/ሠ ነን" አልናቸው። ሽማግሌው ደግሞ "ስለ ኢሕአባ ሰምተናል ግን የደርግ ሰዎች "ኢሕአባዎች ሲሄዱ አይታዩም፣ እንደ ዝንብ ነው የሚበሩት፣ ሁለት የዝሆን የሚያካክሉ ትላልቅ ጆሮዎች አሏቸው፣ ሲተኙም አንዱን ያነጥፉታል፡ ሁለተኛውን ደግሞ ይለብሱታል ብለው ስለነገሩን ነው፡ አሁን ሳያችሁ ግን ገርሞኝ እናንተ'ማ ደርጎች አይደላችሁም ያልኳችሁ፣ ደርጎቹን ትመስላላችሁ ማለቴ ነበር" ብለው አሳቁን።

ለበነገታው ሕዝቡ በምቁን ማርያም ቤተክርስትያን ተሰብስቦ የኢሕአፓን ዓላማ ለመስማት ፍላጎት እንዳለው አሳይቶናል። በዚህም መሠረት አበበ ባርያው አመርቂ በሆነ መንገድ የኢሕአፓ ዓላማ፡ ግብና፡ የፖለቲካ ስራዎችን አርሶ አደሩ በሚገባው ቋንቋ ትምህርታዊ ዲስኩር በማድረግ ያድማጮቹን ስሜት ቀስቀሷል። ትምህርቱ ካለቀና ሕዝቡ ወደየመጠባት ከተመለሰ በኋላ ግን የደርግ ሠራዊት ኢሕአሠን ለመውጋት እየገሰገሰ ነው የሚል ዜና ደረሰን። ሕዝቡም ግልብጥ ብሎ ኢሕአሠን ከቦታው ለማስለቀቅ መሰባሰብ ጀመረ። ከመሃሉ ደጃዝማች ብርሃነመስቀል ኢሕአፓን እንደሚደግፉ ለተከታዮቻቸው ገለጻ አደረጉ የሚል ያልተረጋገጠ ወሬ ሰማን። ወሬው ሓቅ ያዘለ ቢሆንም ኖሮ ኢሕአሠ ከሕዝቡ ጋር መጋጨት ስላልፈለገ፡ በማያሻማ መንገድ ወደ ቤጌምድር ለማፈግፈግ ውሳኔ አደረገ።

ከወሎ ወደ ጎንደር ማፈግፈጉ ግን በገጽ 180 እንደተገለጸው ሳይሆን የሁለቱ ኮማንደሮች፡ ኮሚሳሮች እና አበበ ባርያው ባደረጉት ፈጣን ውሳኔ ነው ሊተገበር የተቻለው። በዚሁ ገጽ አበበ ባርያው "ከዛሬ ጀምሮ በሁለቱም ኃይሎች የሚገኙ ኮሚሳሮች በወታደራዊ ጉዳዮች ጣልቃ ሊገቡ አይገባቸውም ሲል ጥብቅ ማስጠንቀቅያ ሰጠ" የሚለውን እኔ ትዝ አይለኝም፣ ተብሎም ከሆነ ከኢሕአፓ/ሠ አሠራርና መርሕ አንጻር ትክክል አይሆንም። ፓርቲውን ወክሎ የሚሠራው ኮሚሳሩ ነው፣ ኮማንደሩ ደግሞ በወታደራዊ እንቅስቀሴና ጦርነት ጊዜ የበላይነት ይኖረዋል። ነገር ግን "ወታደራዊ ጉዳዮችም" ቢሆኑ የፓርቲውን ዓላማና ግብ የሚጻረሩ ከመሰሉ በደንቡ መሠረት ኮሚሳሩ የበላይነት ይኖረዋል።

'ያልተሳካው ሁለተኛው የውቅሮ ኦፐረሽን' በሚመለከት መጽሓፉ በትክክልና ስእላዊ በሆነ መንገድ ስላስቀመጠው የኢሕአሠን ተሞክሮ በፊልም መቅረጽ ለሚፈልጉ ሰዎች በቀላሉ ማለፍያ ታሪካዊ ሰነድ ማቅረብ ይችላሉ። የውቅሮው ትርምስ፣ ሁካታና ዝብርቅርቅ በመጽሓፉ እንደተገለጸው ነው። ምናልባት ያልተገለጸው ነገር ቢኖር በጦር ሰፈሩ የተሰገሰጉት የደርግ ወታደሮች ደጋግመው "ኢሕአፓ ይወድማል" ብለው ይጮሁ እንደነበር ነው። መጽሓፉ እንደገለጸውም የኃይል 27 ኮማንደር "ሕብስቱ...የጠላትን አምሳ ካሊቨር ቀምቶ አፈሙዙን ወደ ጠላት በማዞር ማጥቃት እንደጀመረ ተሰዋ"። "ንቁ ወታደራዊ መሪዎች መስዋእትነት ከፈሉ። ሕበስቱ፣ የዕብዮ፣ ጌታሁን፣ ዮሴፍና ሮምሐ የውቅሮ ጦርነት ከበላቸው ከኢሕአሠ ንቁ ልጆች ጥቂቶች ነበሩ።"

ከላይ የተጠቀሱትን ጀግኖች በእርግጥ ከፍተኛ መስዋእትነት ከፍለዋል፣ የአሁንና የመጪው ትውልድም ይዘክራቸዋል። እኔ በበኩሌ ለጓዶቼ ከፍተኛ ክብር ነው ያለኝ፣ የተከፈለው መስወእትነት ግን አስፈላጊ አልነበረም የሚል እምነት ነው ያለኝ። የኋላ ኋላ የውቅሮ ኦፐረሽን ሞራላችንን ነክቶታል፣ ስሕተት እንደተደረገም በወቅቱ ተገንዝበን ነበር። በነገራችን ላይ ከዓሲምባ ተነስተን ወደ ውቕሮ በምንሄድበት ጊዜ ሕብስቱ "እኔ እንጃ ዛሬ የምመለስ አልመሰለኝም" በሎኛል፣ እኔም "እንዴ፣ አይዞህ እንመለሳለን" አልኩት። ከዛ በኋላ ጦርነቱ ተጀመረ፣ ውቕሮ በመትረየስ ጋየች፣ ግንኙነት (command and control) ጠፋ። ካፈገፈግን በኋላ ሕብስቱን ብናፋልግ ልናገኘው አልቻልንም፣ ጀግናው ለካ በጦር ሰፈሩ መሃል ሜዳ ወድቋል። እሱ ትክክል ነበር፣ እኔ ስሕተተኛ።

በገጽ 186 የጸሎቴ ህዝቅያስ ባለቤት ሰላማዊት በሕመም ምክንያት እንደሞተች ተገልጿል። ሰላማዊት የሞተች ጊዜ አጋጣሚ ሆኖ በስራ ምክንያት ወደ ቆሎ ማሽላ አካባቢ ዘልቄ ሰለነበር ጓዴና ጓደኛየ የሆነውን ጸሎቴን ላጽናና ብዬ በነበረበት ቤት ጎራ አልኩኝ። ሁለታችንም ስቅስቅ ብለን አለቀስን። ታድያ ምን ዋጋ አለው ጸሎቴም ተከትሏት ሄደ። ከገጽ 210 እስከ 212 የጸሎቴን አሟሟት ያስከተለው ውዝግብ በመጽሓፉ ተገልጿል። ያኔ እኔና ጓዶቼ ደብረ ዳሞ አጠገብ ነው የነበርነው እና ስለ ጸሎቴ ሞት ሲነገረኝ እጅግ በጣም አዘንኩኝ፣ ወድያውኑም ለዳዊት ስዩም ደብዳቤ በመጻፍ ያገዳደሉ ምክንያትና ሁኔታ ጽፎ እንዲልክልኝ ጠየቅኩት። ዳዊት ግን መልስ ሳይሰጠኝ ቀረ። ነገር ግን ዳዊት የጸሎቴ ሞት ከኔ በላይ እንደሚያሳዝነውና እንደሚያሰቃየው ኋሊናየ ተግንዝቦት ነበር። ከብዙ ጊዜ በኋላ ከዳዊት ጋር ሮም (ኢጣልያ) ውስጥ ተገናኘን እና "ጸሎቴ ከሞተ በኋላ የጻፍክልኝ ደብዳቤ ምንጊዜም አልረሳትም" ብሎኛል።

በገጽ 189-90 ከሜዳ ስለጠፉት የትግራይ ተወላጆች የኢሕአሠ አባላት ተጠቅሷል። እነዚህ የጠፉት ግለሰቦች ግን በጋራና ባንዳፍታ ሳይሆን በተለያየ ጊዚያትና በተናጠል ነበር ወደ ኤርትራ የጠፉት። የጠፉት ጓዶች በድርጅታቸው የነበራቸውን እምነት እየመነመነ ስለመጣ እንጂ የኢሕአፓን ዓላማ በመጻረር አልነበረም። በነገራችን ላይ ለመጽሓፉ አስተወጽኦ ካደረጉት ተራኪው አማኑኤልም ከጠፉት አንዱ ነው። ከኔ ጋር ዛለምበሳ አድረው በመንፈቀ ሌሊት ጠፍተው የሄዱ ጓዶችም ነበሩ፣ ማልዳ ስነሳ የሉም፣ ሰለሆነም ከዛላምበሳ ወደ ምድር ሩባ እና ሰብያ የሚያቋርጠውን መንገድ ብቻየን ተወዛወዝኩት።

በገጽ 187 እስከ ገጽ 196 የኃይል አምስት መቶ ታሪክ ተተርኳል፣ ከሞላ ጎደል ስለ ኃይሏ የግብረ ኃይል ሚናና በነበለት አከባቢ ያጋጠማትን ችግር በዝርዝር ተጽፏል። የኃይል 500 ችግር አብዛኞቻችን ያወቅነው ጉዳይ ነበር። እኔ የማላውቀው ነገር ቢኖር በገጽ 191 ተሰፋዬ ቸንቶ ስለ መምህር ደመወዝ (ደሞዝ)

ገረመ "ከህወሓት ጋር የሚጻጻፋቸው ደብዳቤዎች ተይዞበታል ተብሎ እንደታሰረ" እና "ከብርሃነመስቀል ረዳ የሕቡእ ግንኙነት ያደርጋል ሲል ድርጅቱ ይጠረጥረው ኖሮ ወደ ሰንገደ ወርዶ 'አንጃ' ተብለው ከተወነጀሉት አባላት ጋር ወደ መጨረሻ እርምጃ ተወስዶበታል" የሚለውን ነው።

ከገጽ 199 ጀምሮ መጽሓፉ ስለ ከለዓሳ ሰሚናር ያትትና በገጽ 202 "በጸረ ድርጅት ተግባር የተጠረጠሩት የሠራዊትና የፓርቲ አባላት በ ኣቦይ ምስግና ግቢ በተካሄደው ሰሚናር ተጋልጠው በቍጥጥርነት ዋሉ" ካለ በኋላ "ሰንገደ ከደረሱም በኋላ በሁለት ተከፍለው ታሰሩ" ይልና በገጽ 202 እና 203 ደግሞ በአንድ ቡድን 11 ጓዶች በሁለተኛው ቡድን ደግሞ 9 ጓዶች የታሰሩትን ስሞችን ዘርዝሮታል።

ስለነዚህ የታሰሩ ጓዶች ሠራዊቱ እምብዛም አያውቅም ነበር። ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ግን በአንደኛው ቡድን ከተጠቀሱት ጓዶች፡ ለምሳሌ ጌታሁን ሲሳይ በክፍለ ዜና መቆየቱን ነው የማውቀው። እኔ ክፍለ ዜናን ትቼ ወደ ኃይሎቹ ከተቀላቀልኩ በኋላ ምናልባት ከሌሎቹ ጓዶች ቀላቅለው አስረውት እንደሆነ የማውቀው ነገር የለም። በሁለተኛው ምድብ ደግሞ ስማቸው ከተዘረዘሩት ጓዶች፡ ለምሳሌ ብርሀኑ ነጋ እኔ እስከማውቀው ድረስ ከኃይል 27 እንዲቆይ መደረጉ ነው፣ ከኃይልዋ ትንሽ ከቆየ በኋላ ደግሞ "በነጻ ተለቆ ከሠራዊቱ እንደሚሰናበት" ነበር የተነገረን። ምናልባት እኔ የማላውቀው ነገር ቢኖር ብርሃኑን ከሰንገደ እስር አስወጥተው ወደ ኃይል 27 አምጥተውት ሊሆን ይችላል። ወይም በገጽ 205 ግዛው ለገሰ እንደዘገበው ከሆነ ራሱ፡ ብርሃኑ፡ ሮብሌ፡ ክፍሌ፡ ዘመናይ ባሕታ፡ ዳምጠው፡ ያሬድ፡ እና ሓዲሽ በገለብ ትእዛዝ ነጻ ተለቀው ሊሆኑ ይችላሉ።

ምዕራፍ አምስት ኢ.ሕአሠ/ኢ.ሕአፓ ከተሓሐ (ELF)፡ ህግሓኤ (EPLF) እና ህወሓት (TPLF) የነበረውን ግንኙነት ነው የሚያትተው። በዚሁ ምዕራፍ በገጽ 215 አቶ ወልደአብ ወልደማርያም ኢትዮጵያውያን ተጋዳዮችን አስመልክቶ የሰጡት ትችት እጅግ በጣም አስገርሞኛል። ጸሐየ እንደዘገበው ከሆነ አቶ ወልደአብ እንዲህ ብለው ተናግረዋል፦ "ከእናንተ ድርጅት ውስጥ ብዙዎቹ የትግራይ ተወላጆች እንደሆኑ ይታየኛል። ይህ ደግሞ የእናንተ ትግል እየተስፋፋ በሄደ ቍጥር በኢትዮጵያና በኤርትራ ባሉት ትግርኛ ተናጋሪ ሕዝቦች መካከል የትግራይ ትግሪኝ ሥነ ልቦና ስለሚያሳድግ ለምንታገልለት የኤርትራ ነጻነት ዓላማ እንቅፋት ሊሆን ይችላል። ከእዚህም አንጻር እንኳንስ ልንተባበራችሁ ነጻ ባወጣነው ምድርም እንድትንቀሳቀሱ አንፈቅድም" ብለው ነበር" (215-216)። የገረመኝ ነገር ቢኖር እኚህ ብልህ ሽማግሌ ምንም እንኳ ለኤርትራ ነጻነት አስተወጽኦ ቢያደርጉም ትውልዳቸው ግን ከትግራይ ስለመሆኑ ነው። እኔ በፖለቲካ አቋማቸው ላይ ምንም ቅሬታ የለኝም፣ መብታቸው የተጠበቀ ነውና። ኢትዮጵያዊ ሆኖ ኢትየጵያን የሚቃወም ግን ሚስጢሩ ምን እንደሆነ በፍጹም ሊገባኝ አይችልም።

በገጽ 218 የተሓሔ መሪ መልአከ ተኽለን አስመልክቶ ጸሐየ "በኢ.ሕአፓ ላይ ብርቱ ጥላቻ እንደነበረው ብዙዎቻችን እናውቅ ነበር" ያለውን ትክክል ነው የሚል እምነት አለኝ። ይኸም ያልኩበት ምክንያት ኢ.ሕአሠ በርካታ ጠበንጃዎችና ልዩ ልዩ የጦር መሳርያዎችን ተሓሔ በሚቆጣጠረው የኤርትራ መሬት ካስገባ በኋላ ጀብሃዎቹ ያስቀሯቸው የበልጂክ ጠበንጃዎች ነበሩና ከተሓሔ አመራር ጋር ተነጋግረን እንድንረከባቸው እኔ፡ ጋዙ እና ያሬድ ከዓሲምባ ወደ ሓዋሻይት (ባርካ) ወረድን። ክእነ ተስፋይ ደጊጋ፡ መልአከ ተኽለ እና ዓብደላ ኢድሪስ በጉዳዩ ከተነጋገርን በኋላ በእሺ ነገ ብዙ ቀናት ስላስጠበቁንና ቆይታውም የሚራዘም ስለመሰለን ደብዳቤ ወደ ዓሲምባ ጓዶች እንጻፍ ብለን የቆይታችንን ምክንያት የሚገልጽ ደብዳቤ ላክን። ደብዳቤ ከሐዋሻይት ወደ ዓሲምባ የሚላከው በጀብሃ ድኅንነት (ክፍሊ ጸጥታ) በኩል

ነው። ነገር ግን የአደራ ደብዳቤ መሆኑ ቀርቶ ከፍተው ስላነበቡት መልአከ ላነጋግራችሁ እፈልጋለሁ አለ፣ እሺ እንነጋገር አልነው፣ የበልጅኩን ጉዳይ የሚነጋገር መስሎን። እሱ ግን "ለምንድነው አዬዎች ያላችሁን" አለ። "አረ እኛ እናንተን አዬዎች አላልንም" አልነው፣ "ይኸው ደብዳቢያችሁ ምስክር ነው" ካለ በኋላ የተነበበውን ደብዳቢያችን አሳየንና ባውራጣቱ እያመላከተ "ብዙ አዲዎች አልፈን ስለምንሄድ መዘግየታችን አይቀርም" የሚለውን አነበበና "ይኸው አጼዎች አላችሁን" አለ ደጋግሞ፣ "እዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ አዬዎች የሚል የለም" አልኩት። ምስኪኑ መልአከ 'አዲዎች' የሚለውን ለካ 'አዬዎች' ብሎ አንብቦታል። 'አዲዎች' ነው ብዬ ላሳምነው ስሞክር ግትር ብሎ "በአማርኛ አዲዎች ይባላል እንዴ?" ብሎ መለሰ፣ እኔም "አይባልም፡ ግን ኢሕአሠ በዘልማድ አንድአንድ የትግርኛ ቃላት ይጠቀማል፡ ለምሳሌ ታዕሊም፡ ተበገስ ወዘተ፣ በዚሁ ደብዳቤም 'አዲዎች' ስንል 'መንደሮች' ማለታችን ነው" አልኩት።

እኔና ጓዶቼ መልአከና ዓብደላ ኢድሪስ ቤልጅጎቹን ላለመመለስ የጠነሰሱት ሴራ ነበር የመሰለን። ምናልባት ግን ሻዕቢያዎች የጀብሃ አመራሮችን 'ራእስታት ጀብሃ' (የጀብሃ ራሶች) ይሏቸው ስለነበር በውስጠ ኀሊናቸው 'ራእሲ' እና 'አዬ' አገናኝተውት ሊሆኑ ይችላሉ። ያም ሆኖ ይህ እኛ ሳይቀናን ወደ ዓሲምባ ተመለስን፣ ንብረቱም ቀልጦ ቀረ። በገጽ 219 ዳዊት የተሓኤ አመራር አባላት "ከኢሕአፓ አመራር አባላት ጋር መነጋገር እንደሚፈልጉ... ደጋግመው የሚያቀርቡልኝ ጥያቄ ነበር" ያለውን ለኛም ተመሳሳይ ጥያቄ ቀርቦልን ስለነበር ምናልባት በዚሁ ምክንያትም ብረቱን እንደ ቅድመ-ሁኔታ ተጠቅመውበት ይሆናል።

በገጽ 226 በ1969 (1977) በተደረገው የሕግሓኤ የመጀመርያ ድርጅታዊ ጉባኤ ከልዩ ልዩ አገሮች የፓርቲና አገር ተወካዮች ማለትም ከግብጽ፡ የመን፡ ኢራቅ፡ ኢጣልያ፡ ጀርመን፡ እንዲሁም የኢሕአሠ አመራር ተገኝተው ነበር። "ኢራቅን ወክለው የተገኙት የቀድሞ የውጭ ጉዳይ ሚኒስተር ታሪክ ዓዚዝ ነበሩ።" እኔና ጓዶቼ ወደ ዓሲምባ ከመዝለቃችን በፊት ሳሕል ውስጥ በቆየንበት ጊዜ ከኢራቅና ሲርያ የመጡ የመንግሥት ተወካዮች አይተን ነበር። ያኔ እንደሰማነው ከሆነ በእርስ በርስ ጦርነት ይጠፋፉ የነበሩትን ሻዕቢያና ጀብሃን ለማስታረቅ ነበር የመጡት። ያም ሆኖ ይህ፡ ዓረቦች በከፍተኛ ደረጃ በኢትዮጵያ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ በመግባት ሙሉ በሙሉ የኤርትራ ግንባሮችን ይደግፉ ነበር። በዛን ጊዜ የኃይለሥላሴ መንግሥት የኤርትራ ግንባሮች እንቅስቃሴ ከዓረብ ጸረ-ኢትዮጵያ ፖሊሲ የተቆራኘ ነው በማለት ሲገልጸው የኢትዮጵያ የግራ ኃይሎች (የተማሪ ንቅናቄ፣ኢሕአፓ ወዘተ) ከመጤፍም አልቆጠሩትም ነበር። ሓቁ ግን የኃይለሥላሴ መንግሥት ያለውን ነው።

በገጽ 235 የነበለት አዛውንት ኢትዮጵያውነታቸውን ለማረጋገጥ የሰጡት ምክር በተለይ ባሁኑ ጊዜ የጎሳ ፖለቲካ ለነካካው ወጣትና አዋቂ ይማርበት ዘንድ (ፍላጎቱና ንቃቱ ካለ) እንዳለ ከመጽሓፉ መጥቀሱ አስፋለጊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። እኝህ አዛውንት ለማስተላለፍ የፈለጉት መልእክት የግላቸው አመለካከት ያዘለ ብቻ ሳይሆን ያብዛኛው የትግራይ ሕዝብ የማያወላዳ አቋምም የሚያስተናግድ ነው፡-

"በ1969 ዓ.ም. አጋማሽ አካባቢ በእምባ ሰነይቲ ሽምዕጭ ተብሎ በሚጠራው መንደር የህወሓትና የኢሕአሠ አባላት ሕዝቡን ለመቀስቀስ ተገኝተው ነበር። ሁለቱም ቡዱኖች የድርጅታቸውን ዓላማ ካስረዱ በኋላ የአከባቢው አዛውንት ማሳረግያውን ንግግር አደረጉ። አዛውንቱ መሄድ የሚሳናቸው ስለነበሩ ሰዎች ደግፈው ወደ በቅሏቸው እንዲያወጧቸው ከጠየቁ በኋላ የሚከተለውን ንግግር አደረጉ። ወደ ህወሓት አባላት እጃቸውን ዘርግተው 'እናንተ ከሆዳችን የወጣችሁ ልጆቻችን ናችሁ' ወደ ኢሕአሠ አባላትም ፊታቸውን አዙረው 'እናንተ ደግሞ ከሁሉም የኢትዮጵያ

ግዛት መጥታችሁ ለኛ ስትሉ ነው የምትታገሉት። የሆነውን ሆኖ እኛ የትግራይ ሰዎች ሆነን ስንቀር ኢትዮጵያ ከማን ጋር ልትቀር ነው? ስለሆነም እኛ ኢትዮጵያ ከሚል ጋር ነው የምንወግን' ሲሉ ሐሳባቸውን ሰነዘሩ።" (ገጽ 235)

በገጽ 238 የሕዝባዊ ግንባር ተወካዮች ህወሓት እና ኢሕአፓን ለማስታረቅ በሚል መንፈስ ባራኪና ዶክተር እዮብን ልከው እንደነበር ተጠቅሷል። እኔም በ1995 እአአ በጻፍኩት መጽሓፍ ውስጥ ገልጩዋለሁ። በተጨማሪም እነዚህ ሁለት የሻዕብያ ተወካዮች "የኢሕአፓን አመለካከት የሚደግፉ ይመስሉ ነበር" ተብሏል። ሁለቱ ግለሰቦች ተራማጅ እንደነበሩ እኔም የማውቀው ነገር ነው፣ ኢሕፓንም በግላቸው ደግፈው ሊሆኑ ይችላሉ። ድርጅታቸው ግን በዛን ጊዜ ወደ ህወሓት (ወያኔ) ያደላ ይመስለኛል።

በገጽ 239 "በነበለት አካባቢ ካሕሳይ የሚባል ጠንካራ የኢሕአፓ ሚሊሽያ በሕወሓት አባላት ተገደለ" የሚለውን ከሞላ ጐደል ትክክል ሆኖ፣ የማስታወስ ችሎታየ ካልቀነሰ በስተቀረ፣ ካሕሳይ መጀመርያ የወያኔ ሚሊሽያ ነው የነበረው፣ ከድርጅቱ በነበረው ቅራኔ ህወሓትን ትቶ ከኢሕአፓ/ሠ ስለተቀላቀለ የህወሓት አባላት በጥሞና ሲከታተሉት ከቆዩ በኋላ መልካም አጋጣሚ ሲያገኙ አጠፉት። በገጽ 240 በተመሳሳይ መልኩ ሁለት ጓዶች ማለትም ስሙር በታሕታይ ሩባ፣ ታደሰ ደግሞ በእምባሰነይቲ በህወሓት መገደላቸውን ተገልጿል። እኔም በመጽሓፌ የሁለቱ ጓዶች መገደል ጠቅሼዋለሁ።

ከገጽ 236 እስከ 241 በህወሓትና በኢሕአሠ በተደጋጋሚ ዘጠኝ የድርድር ስብሰባዎች መደረጋቸውን መጽሓፉ በትክክልና በሚገባ ገልጾታል። 9ኛው ስብሰባ በየካቲት 19፣ 1970 በሰብያ (ሱሩኸሶ) እንዲደረግ ቢታቀድም "የሕወሓት ተወካዮች ሳይመጡ ቀሩ።" "በመሃሉ አንድ የሕወሓት አባል በኢሕአፓ አባል ተገደለ። በየካቲት ወር በ1970 ዓ.ም. የኢሕአሠ ኃይል 14 ወደ ቤዝ አምባ በምትጓዝበት ወቅት በአንዲ ጋንታ አይረ ወንዝ ላይ አንዲት የሕወሓት ኃይል በደፈጣ ተኵስ ከፍታ ጦርነት ተካሄደ።" ይህ ከሞላ ጎደል ትክክል ሆኖ ሳይጠቀስ የታለፈ ነገር ቢኖር ግን የህወሓት ኃይል የማጥቃት እርምጃ ከመሰንዘሯ በፊት የኃይል 14 ጓዶች የታጠቀ ኃይል ወደነሱ መጠጋቱን ከተነገዘቡ በኋላ የይለፍ ቃል ጠየቁ። የህወሓት ተጋዳዮች ደግሞ "ኃይል ሦስት" ብሎው መለሱ። የኢሕአሠ ኃይል ሦስት ከሌሎች ኃይሎች ተዋቅራ መጥፋቷን ጓዶቹ ስለሚያውቁ ወድያውኑ ቦታ (ተሸክል) ያዙ፣ ግን ከመቅጽበት በህወሓቱ ኃይል ተኵስ ተከፈተና ጦርነቱ ተፋፋመ። ጦርነቱ በሚካሄድበት ጊዜ የሰብያ ማርያም ቤተክርስትያን ካህናት ጸሎትና ቅዳሴ ማሳረግ ጀመሩ፣ የኃይማኖት መሪዎቹ 'የሰላሙ መንገድ ይሻላል' የሚል መልእክት ለማስተላለፍ ነበር የሞከሩት።

ካህናቱ ብቻ ሳይሆን ያካባቢው ሕዝብና ጠቅላላ የትግራይ ሕዝብ ኢሕአሠንና ህወሓትን ለማስተናገድ ፍላጎት እንዳለውና ከተቻለም በአንድነት እንዲታገሉ፣ ካልሆነ ደግሞ እርስ በርሳቸው አምባጓሮ ሳይጭሩ ደርግን እንዲመቱ ነበር የሚፈልገው። የህዝቡ ፍላጎት ሚዛንና ግምት ሳይሰጠው ቀረና ኢሕአሠና ህወሓት በጦርነት ተዘፈቁ። ከላይ እንደተጠቀሰውና መጽሓፉም እንዳስቀመጠው የመጀመርያው ጦርነት በዚሁ በሰብያ አከባቢ ነበር፣ የህወሓቱ ኃይል የዘነጋው ነገር ቢኖር ግን ጦርነቱ በኢሕአሠ ቤዝ አምባ መካሄዱ ነው። ለዚህም ነው ሁለት የኢሕአሠ ኃይሎች ወድያውኑ መጥተው የኃይል 14ትን ያጠናከሩትና የህወሓትን ኃይል የከበቡት። የህወሓቱ ኃይል መሪ በዚሁ ጦርነት ቆስሏል፣ ኃይሏም መዳከም ስለጀመረች አማራጩ ማፈግደግ ብቻ ነበር።

በገጽ 242 መጽሓፉ የኢ.ሕ.አሠ ኃይል 74 “በሕወሓት በተደረገው ድንገተኛ ወረራ” መጠቃቷን ከወሳ በኋላ ይህች ኃይል ከኃይል 27 ወደ ወሎ ተዘዋውራ እንደነበረና ከተመለሰች በኋላ በጠላት ጉዳት እንደረሰባት ይገልጻል። ቀደም ብሎ እንደተገለጸው እኔ የማላውቀው ነገር ከሌለ በስተቀረ ወደ ወሎ የተጓዙት ኃይል 27 እና ኃይል 10 ብቻ ናቸው።

በኢ.ሕ.አሠና ህወሓት የመጨረሻውና የተፋፋመ ጦርነት የተካሄደው በ ብዘት ከተማ ነበር። ከተማው ከ ደብረ ዳሞ ግርጌ ስር ሜዳ ላይ የተዘረጋ ሆኖ ከዓዲግራት ወደ ዓድዋ የሚሄድ አውራ ጎዳና ለሁለት ሰንጥቆት ያልፋል፡ የጭነት መኪናና አውቶቡሶች የሚመላለሱበትና የገበያ መናኸርያም ነው። ከወታደራዊ ስትራተጂ አንጻር ግን የብዘት አቀማመጥ በጣም መጥፎ ነው። በትላልቅ ተራሮች የታጠረ ከተማ ነውና! ስለሆነም ከሜዳው ወደ ተራሮቹ ማፈግፈጉ ይከብዳል። ለዚህም ነው በሁለቱ ሠራዊቶች ዘንድ በርካታ ተጋዳዮች ከጦርነቱ ሳይመለሱ የቀሩት።

ከብዘት ጦርነት በኋላ ኢ.ሕ.አሠ ከማፈግፈግ ሌላ ምርጫ አልነበረውም፣ ማፈግፈጉ ግን የተቀነባበረ አልነበረም፣ ሊሆንም አይችልም ነበር፡ ምክንያቱም የኢ.ሕ.አሠ ኃይሎች ወደ ዓሲምባ በሚያመሩበት ጊዜ የህወሓት ኃይሎች ተከታትለው በመምጣት ጦርነት መቀጠል ስለፈለጉ ነው። በዚህም ጊዜ ከዛም ከዚህም የተሰባሰበው የኢ.ሕ.አሠ ተጋዳይ እየተከላከለ ማፈግፈግ ጀመረ።

በገጽ 247 እንደተገለጸው ጎይተሎ አካባቢ የመከላከል ጦርነት ያካሄደችው አንዲቷ የኢ.ሕ.አሠ ጋንታ መሪዎችዋ እንኳ በመስዋእትነት ቢያልፉም በህወሓቱ ሠራዊት ግን ከፍተኛ ጉዳት አድርሳለች። ከዚህ በኋላ ከየአቅጣጫው የመከላከልና የማፈግፈግ ስልት የያዘው የኢ.ሕ.አሠ ሠራዊት ወደ አንድ አቅጣጫ ማለትም ወደ ሽመዛና (ኤርትራ) ማፈግፈግ የግዴታ ሆነ። በገጽ 250 እንደተመለከተው “በዚሁ ጦርነት አጨራረስና ወደ ኤርትራ ማፈግፈጉ ማን እንዳዘዘው የብዙዎቹ ጥያቄ ነው” የሚለውን እውነትነት ያለው ነው። ነገር ግን አንድ እኔ ትዝ የሚለኝ ነገር ቢኖር ጓድ አበጀና ሌሎችም አመራሮች በነበሩበት ምን ይሻላል፡ ወደ ኤርትራ ማፈግፈጉ ወይስ ወንዙን ተከትሎ፡ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ ይዞ፡ ትግራይን ሰንጥቆ ወደ ቤጌምድር መግባት? በሚል ውይይት ተካሂዶ ነበር። ሁለተኛው አማራጭ ከደርግና ከህወሓት እንቅስቃሴ አንጻር እንደማያዋጣ ታይቶ አንደኛው አማራጭ የተሻለ ሆኖ ስለተገኘ ሠራዊቱ ወደ ኤርትራ እንዲያመራ ተደረገ። ይህ በቀውጢ ጊዜ የተደረገ ውሳኔ ስለሆነ የሠራዊቱ አመራር የበላይ አካል ትእዛዝ መጠበቅ የማይቻልበት ጊዜ ነው የነበረው። እነ ደብተራውም ቢሆኑ በቦታው አልነበሩም፣ ሠራዊቱ ወደ ኤርትራ ጉዞውን ዚጀምር ነው የተቀላቀሉት። በመጽሓፉ እንደተጠቀሰው ግን በእርግጥ “አንዲት ጋንታ ትግራይን መሓል ለመሓል ሰንጥቃ ቤጌምድር ከሚገኘው የኢ.ሕ.አሠ ሠራዊት ተቀላቅላለች።”

ሌላ የማልረሰው ትዝታ ቢኖር ኢ.ሕ.አሠ ወደ ኤርትራ ካፈገፈገ በኋላ የተደናገጡና ያዘኑ የዓዲ ኢ.ሮብ አዛውንት ተከትለውን ሽመዛና ድረስ መጡ። ከነዚህም አንዱ ኣቦይ ደበሳይ፡ የዶ/ር ተስፋይ አባት ናቸው። እቤታቸው ድረስ እየሄድን የማክያቶ ዓይነት ቡና አንጠጣ ነበር፣ ዶ/ር ተስፋይ ለመስዋእትነት ራሱን ከገደለ በኋላ ኢ.ሕ.አሠ በዓሊቴና የቀብር ስነሥርዓት (ካልኣይ ቀብሪ) አድርጎለት ስለነበር ኣቦይ ተስፋይ ልጃቸው ጀግና እንደሆነና እንዳልሞተ ተናግረው ነበር። ለሠራዊቱ ከፍተኛ ፍቅር ስለነበራቸው ደግሞ ተከትለው ሽመዛና ድረስ መምጣታቸው የሚያስገርም አይደለም። ሊሰናበቱ የመጡ መስሎን ታድያ “እንግዲህ እንዳይመሽብዎ ይመለሱ” ስንላቸው፣ “አይ ከናንተ ጋር ነው የምሄደው” አሉ። ከስንት ልመናና ማግባባት በኋላ ግን ተመልሰው እንደሚሄዱ አረጋገጥሉን።

የሆኖ ሆኖ ኢሕአሠ በተሓሔ ተባባሪነት በጸሮና በኲል የሃዘሞን በረሃ አቋርጦ ወደ ቅናፍና ከዛም ወደ ዓረዛ፡ ቀጥሎም ወደ ቆላ ሰራየ ዘልቆ፡ ሻምብቆን አልፎ፡ ሃይኮታን ወደ ግራ ትቶ ሸምሸምያ በተባለው በተከዘ ጠረፍ የሚገኝ የቤጌምድርና የኤርትራ አዋሳኝ ስፍራ ጊዜያዊ ቤዝ አምባ (ጦር ሠፈር ያለ ጠበንጃ) ተመደበለት።

በሸምሸምያ የኢሕአሠ ሠራዊት ወደ ስደተኛ ተጋዳይ ተቀየረ፣ ምግብ እጥረት ስለነበረም ሕይወትን የማትረፍ ስትራተጂ መቀየስ ነበረበትና በአካባቢው የተገኘውን መብላት ጀመረ። እስከሚሰለቸን የበላነው ነገር ቢኖር ሓምሊ ዓለምን (የዱር ጎመን) ነበር፣ ሚዳቋና የሜዳ ፍየል በአካባቢው አልነበሩም፣ ቢኖሩም ሠራዊቱ ብረቱን ለጀብሃ ስላስረከበ በአደን ላይ መሰማራት አይችልም ነበር። አንድ ቀን ሲቸግረን እኔና ኃይሌ ቀጭኑ አንበጣ መብላት እንዳለብንና ገንቢ ምግብ እንደሆነም ለጓዶች ለማስረዳት መከርን። ከዱር ጎመኑ ጋር ተመሳስለው የተቀመጡ በርካታ አረንጓዴ አንበጣ ስላየን አንድ ሁለት ለመግለጫ ያህል ከያዝን በኋላ ጭንቅላታቸው መዘን እግሮቻቸውና ክንፎቻቸውን ካሰውገድን በኋላ በእሳት ጠበስ ጠበስ አድርገን መብላት ጀመርን። አረንጓዴ አንበጣ (የማርያም ፈየልም ይባላል) በ20ና በ30 ቡድን፡ ግፋ ካለም በ100 ይንቀሳቀሳሉ እንጂ እንደ ቀዩና ብጫው አንበጣ በእልፍ አእላፍ አይበሩም። “ቀዩ ወይም ብጫው አንበጣ ቢመጣልን ኖሮ ከዚህ ከዱር ጎመን እንገላገል ነበር፣ ሠራዊቱም ይጠግብ ነበር” በማለትም ሰበካውን ተያያዝነው። ግን ድል አልተቀዳጀንም፣ እንድያውም በተቃራኒው ከከበቡን ጓዶች መሃል አንድ እንኳ ለይስሙላ አረንጓዴ አንበጣውን የመኰረው የለም። ሀሉም ዘገነናቸው፣ አስቀያሚ ነው አሉን።

የሕይወት ማትረፉ ትግል በሸምሸምያ ቀጠለ፣ አንድ ቀን ግን ያልጠበቅነውን (ምናልባትም በሆዳችን ተመኝተን እንደሆነ አላውቅም) መና መጣልን። አስማማው በመጽሓፉ እንዳስቀመጠው ተከዘ ገጸ-በረከት ይዞልን መጣ። የሞቱ ግመሎችን እንደ ስጦታ አስረከበን። አንዳንድ አባላት አሁንም ቢሆን ቅር ያላቸው ነበሩ፣ በርካታው የሠራዊቱ አባለት ግን ግመሎቹን ተያያዟቸው። የግመለቹ ሞት የኛ ሕይወት ሆነ!

ሌላ ያልጠበቅነውን ነገር በፊታችን የተደቀነ ነገር ቢኖር ደግሞ በዚሁ በሸምሸምያ የተነገረን አሳዛኝ ዜና ነው። ጸጋየ ገብረመድህን (ደብተራ) ሰራዊቱን ሰብስቦ አንጃ ተብለው በተጠረጠሩት ጓዶች ላይ እርምጃ እንደተወሰደባቸው ገለጻ አደረገ። እጅግ በጠም አዘንኩኝ፣ በውስጠ-ኀሊናየም “ቅራኔዎችን በዴሞክረሲያዊ መንገድ መፍታት ካልቻልን ለወደፊቱ በኢትዮጵያችን ዴሞክራሲ ሊሰፍን አይችልም” አልኩኝ። በጣም ያፈቀርኩትና የኢትዮጵያ ብሩህ ተስፋ ነው ብዬ ያቀፍኩትን ኢሕአፓን መጠራጠር ጀመርኩኝ። ስለሆነም ለበነጋታው የስንብት ደብዳቤ ለአመራሩ አቀረብኩኝ። ጓድ ጸጋየ የስንብቱ ደብዳቤ ካነበበ በኋላ ቅር እንዳለው ነገረኝና አከታትሎም “ለመሆኑ መቼ ነው መሄድ የምትፈልገው፣ እዚሁ ልትቀር ነው ወይ” አለኝ፣ “በፍጹም እኔ ሠራዊቱን ትቼ አልሄድም፡ ቤጌምድር ገብተን ከሠራዊቱ ጋር ከተቀላቀልን በኋላ ነው ስንብቱን የምፈጽመው” አልኩት።” “ጎሽ!” አለና ተያይዘንም ቤጌምድር ገባን።

በኢሕአፓ/ሠ ውስጠ-ደንብ መሠረት ማንኛውም የፓርቲውና የሠራዊቱ አባል ስንብት ከጠየቀ/ች መብቱ/ቷ የተጠበቀ ስለነበር መጨረሻ የተሰናበትኩ ጊዜ የጠቅላይ አመራር ኮሚቴ (ጠአኮ) አግኝቻቸው ነበር። ጓድ አበጀ (አለማየሁ አስፋው) እና ጓድ ዳዊት ደስ ባይላቸውም ቅሉ “ደህና ሁን፡መልካም ዕድል” (ቃላቶቹን በደንብ አላስታውሳቸውም) ብለውኛል። ድበተራው ግን በኤርትራ

መሬት ውስጥ “ጎሽ” ያለኝ ጓድ ሊያናግረኝም አልፈለገም። አልተቀየምኩትም! መማረኩንና ጉዳት እንደደረሰበት ከሰማሁኝ በኋላ ደግሞ በጣም አዘንኩለት፣ የፈለገውን ልዩነት ይኑር አብረን ለአንድ ዓላማ ተሰልፈናልና!

ከዓዲ ሰላም አካባቢ ብቻየን መንገዱን ተያያዝኩት፣ ኪሴ ውስጥ ድርጅቱ የሰጠኝ አስር ብር ብቻ ነው ያለኝ። ከ ማይ ጸብሪ አውራ ጎዳናውን አቋርጬ ወደ ዋልድባ (ቆላ ወገራ አካባቢ) በማምራት ላይ እያለሁኝ ሁለት ጓዶች ከማዶ አየሁኝና ስጠጋቸው ጌታቸውና ሶስና ናቸው። ወዴት ናችሁ ስላቸው፣ ተሰናብተናል አሉኝ። ደስ አለኝ፣ ደስታው ግን ከስንብታቸው የመነጨ ሳይሆን፣ አብሮ የመሆን የሰው ባህርይ ፍላጎት (desire of companionship) ስለተሟላልኝ ነበር። ወደ ዋልድባ እንደተጠጋንም ሌላ ጓድ አየን፣ እሱም ተሰናብቷል፣ ገ/እግዚአብሔር (ዘኬዎስ) ነበር። አራታችን ተያይዘን ዓዲ ረመጽ (የወልቃይት ወረደ ከተማ) ደረስን፣ ከዛም ቃፍትያ ገባንና በሑመራ ጀዲዳ (አዲስ ሑመራ) አቋርጠን ደግሞ ገዳርፍ/ሱዳን ገባን። በመከታተል ብዙ ጓዶች ተሰናብተዋል። ቆይተውም ከአመራሩ ሳይቀሩ ተሰናብተው ወደ ሱዳን ገቡ። ከነ አበጀና ከነሮባ እንደገና በአካል ካርቱም ውስጥ ተገናኘን። ከዕለታት አንድ ቀን እኔና ዓለም (ከጀርመን ድርጅቱን የተቀላቀለ) ካርቱም መሃል ከተማ ስንዘዋወር ሮባን አገኘነውና “መሄዴ ነው፣ ግን ክህደት ይሰማኛል” - በእንግሊዝኛ sense of betrayal ነበር ያለው - አለና ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። በገጽ 28 ሮባ ራሱ እንደዘገበው “...የመሐመድ ማሕፉዝና የብንያም አዳነን መሰዋት ነግሮን አለቀስኩ። ከዛ በኋላ ያለቀስኩት ድርጅቱን ለቅቄ ስወጣ ብቻ ነበር” ያለውን እውነት ብቻ ሳይሆን ከላይ እንደጠቀስኩት ፊቱ በእንባ ሲጥለቀለቅ አይቼዋለሁ። የዓይን ምስክር ነኝ።

ይህ መጽሓፍ የኢሕአሠ አባላት ለነበሩ ጓዶች ትዝታ፣ ለተሰዉት ደግሞ ሓወልትና ወመዘክር ነው። ይህ የታሪክ ቅርስ ከትውልድ ወደ ትውልድ መተላለፍ ስላለበት በኢሕአፓ/ሠ ዙርያ ተሰማርተው የነበሩት አሁን በሕይወት የሚገኙ ጓዶች ለአሁኑና ለመጪው የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ቅርሱን ማውረስ ገዴታቸው መሆን አለበት የሚል እምነት አለኝ።

በመጨረሻም በዚሁ ቊም-ነገር አዘል መጽሓፍ አንዳንድ የሰውና የቦታ ስሞችን አሰመልክቶ የስነ-ማኀተም ግድፈቶች አሉና ለወደፊቱ እንዲታረሙ መጠቆም እፈልጋለሁ። እንደሚከተለውም ቀርቧል፦

| ገጽ | ቃሉ | እርማት |
|---|---|---|
| 33 | ግርግር | ገራግር |
| 34 | ጣዕመ | ጠዓመ |
| 46 | ቢሊቃት | ቢሌቓት |
| 61 | አድ አውልዕ | ዓዲ አውሊዕ |
| 61 | ጋይሞ | ጋይም (ጋይም ኃይለሚካኤል) |
| 66 | አላ | ዓላ |
| 68 | ዘሩ | ዘርኡ (ዘርኡ ክሕሸን) |
| 74 | የአድ ኣዋዕላ | የዓዲ አውዓላ |
| 120 | ወረአትለ | ወረዓትለ |

All Rights Reserved. Copyright © Institute of Development and Education for Africa (IDEA), Inc. Dr. Ghelawdewos Araia can be contacted for educational and constructive feedback via dr.garaia@africanidea.org